# ትግል እንደ ሀገሩ

ሚዛን ተካልኝ

ሁለት ሞት ከመሞት፣ ክብርንም ተገፎ
ቢሞቱስ ግድ የለ ፥ ከእምነት ጋር ተቃቅፎ
ጎሊናን ገስፆ
አንጀትንም ገርፎ።
ቢሞቱም ግድ የለ።

ፈቃደ አዘዘ (ጩኸት)

በቅድሚያ ፍርሀት በሰፈነበት የድፍረትን ጮራ የሚፈነጥቁ፣ ዝምታ በበዛበት ግፍ በዛ ብለው የሚጮሁ፡ ግለኝነት በነገሰበት ለሀገርና ለወገን ሊሰዉ የቆረጡ ጀግኖችን መዘከርና ማክበር ተገቢ ነው። ሀገር ወዳድነት አፋዊነትን ማለፍ አቅቶት ሳለ፣ ታጋይም ከትግል ሜዳ ርቆ የሚንጣጣው ሆኖ በተገኘበት፣ ተራ ፍርሀታቸውን ማቸነፍ ያቃታቸው ጦር መሪ ነን ብለው በሚቧርቁበት፣ መስዋዕትነትን የሚደፍሩትን ብርቅዬዎች ማመስገን ግዴታችን ይሆናል። ወደ ርዕሳችን ከመግባታችን በፊት ከፐሮፌሰር አስራት ጀምሮ እነ ተስፋዬ ታደሰን፣ አሰፋ ማሩን፣ ገብረ እግዚአብሔር (ጋይም) ንና ሌሎችንም ዘክረን መምህር የኔሰው ገብሬን ደግሞ በድፍረትህና መስዋዕትነትህ ሀፍረታችንንና ፍርሀታችንን ለራሳችንም አጋልጠሃልና ምስጋ ና ይግባህ ማለት ይኖርብናል ። እንኳን ሊቃጠል የባሩድ ሽታ ካለበት ቦታ በአህጉራት ደረጃ ሸሽቶ ያለው ነውና ዘንድሮ ዋና ተቃዋሚ የሚባለው

ባለፉት አያሌ ዓመታት የትግላችን ቅኝት በወያኔም ሆነ አወቅን ባሉ ግን በተደናገሩ ምሁሮ ች ሲበለሻሽ ቆይቷል። ወደፊት ፈቅ ብለን ድልን ልንጠጋ ያልቻልንበትም አለምክንያት አይደለም። ከመሰረታዊው ማነው ጠላት ጀምሮ በምን ዓይነት ትግል እንሰማራ ከሚለው ድረስ ወያኔ ዕይታችንን እያንሸዋረረ ዋናውን ቁምነገር እንድንስት ሲያደርገን ቆይቷል። ይህ ዛሬም እየቀጠለ ያለ ነው። የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ምን ዓይነት ትግል መደረግ ይገባዋል የሚለውን ምላሽ ሰጪ ሆኖ ሳለ ወያኔ ሕዝብ ጦርነት ሰልችቶታል ያለውን ቀረርቶ ሌሎችም እንደ ገደል ማሚቴ እያስተጋቡ ሰላማዊ ትግል ብቻ የሚል በተግባር ከቶም ሊታይ ያልቻለ ፈሊጥን አንግሰው፥ ጠመንጃ ያነሱትን መላ ያልገባቸው ብለው እያወገዙ ለአፋኙና አረመኔ ው አገዛዝ ድጋፍ ፈለጉ አልፈለጉ ሰጡ ። ትጥቅ ትግል ወይስ የሰላም ትግል በሚል አላስፈላ ጊ ንትርኩ ሲጦፍና ወያኔም የተቃወሙትን ፀረ ሰላም እያለ ሲገድል ወርቅ ጊዜ አለፈ ። ተጨባጩን ሁኔታ በተለይም የወያኔ አገዛዝን ጠባይና ምንነት በዝርዝር መመርመር ሲገባ

ይህ ባለመደረጉ ወያኔ ሀገር ወዳድ የመሰላቸው፣ ዴሞክራሲ መርሆችን ይቀበላል፣ አደብ ይገዛል ወዘተ ብለው ያመኑ ጥቂቶች አልነበሩም። በመሆኑም በወያኔ ላይ ትጥቅ ትግል ሊጀምሩ የሞከሩት ሀይሎች ውግዘትን እንጂ ድጋፍን አላተረፉም። አልፎ ተርፎ ግን የሰላም ትግል ያሉት፣ ከዱላ ይልቅ መላ ብለው የሰበኩት አንዲትም ቀን ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የተቃውሞ ሰልፍ ሲያደርጉ ወይም በሌሎች ሀገሮች እንደታየው ሲታሰሩ አላየንም። ስለ ሰላማዊ ትግል ሰሊፈፍ፣ ወያኔ ታጋዩን ሲቀጥፍ፣ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ደብዛው ጠፍቶ ውዥንብርና ቀቢፀ ተስፋ ሲሰፍን ወያኔ እሰየው ብሎ እየገደለና ሀገርን እያደማ እያቆሰለ ለሀያ ዓመት እነሆ ቆይቷል።

በኢትዮጵያ አካባቢ ሀገሮች የነፈሰው የሕዝባዊ አመፅ ሀገራችንንም ሊነካ መቻሉ በግልፅ እየታየ ነው። የወያኔ ዕድሜ ረጅም አይደለም። ወያኔ ራሱ በውስጣዊ ቀውስ የታመሰ ሲሆን ሕዝብም ሁኔታው መሮት ለውጥ ወይ ሞት ወደሚልበት ጫፍ ደርሷል። የቀረው ያልተሟላው ሁኔታ ትግሉን አቀናብሮ የሚመራ ሀይል ወይም ሀይሎች አሊያም ያበጠውን የሚያፈነዳ ነው። የታመቀውን የሕዝብ ቁጣ ምን ያፈነዳው ይሆን የሚለው እንዳለ ሆኖ ፍንዳታው ግን የወያኔን መጨረሻ የሚያመጣ መሆኑ የሚታይ ነው። በተጨባጩ የኢትዮጵያ ሁኔታ የሕዝብ የተደራጀ ትጥቃዊ ፍልሚያ ሆነ ሰሜን አፍሪቃና በመካከለኛ ምስራቅ እንደታየውና እየታየ እንዳለው ያመረረ ሕዝባዊ አመፅ ሊካሄድ ይችላል/ይገባልም ። ሁኔታው ግድ የሚለው ነው። ይህን በተመለከተ ግን ማወቅና መገንዘብ ያሉብን መሰረታዊ እውነታውች አሉ።

1ኛ/ ሕዝባዊ አመፅ ብንልም የሀገራችን ሁኔታና በቅርቡ አመፅ የተካሄደባቸው ሀገሮች ሁኔታ አንድ ዓይነት አይደለም። አምባገነናዊ አገዛዞች መኖራቸው ቢያመሳስላቸውም ተጨባጭ ሁኔታዎቻቸው ለየቅል ናቸው። ለምሳሌ በቱኒዝያ አንድ ዜጋ በተቃውሞ ራሱን ማቃጠሉ በቱኒዝያም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተስተጋብቶ ለቱኒዝያ ሕዝብ ትግል አቀጣጣይ ቢሆንም የመምህር የኔሰው ገብሬ መስዋዕትነት ግን በዚህ ዓይነት ጫና የሚያደርግ አይመስልም ። አምፁ ብሎ ቀስቃሽነቱ እንዳለ ሆኖ። ራሱን ከማጥፋት ምን አለ አንዱን ቱባ ወያኔ ገድሎልን ቢሞት ያሉ ብዙ ናቸው። ሕዝባችንን ምን ይቀሰቅሰዋል የሚለውንና ለገዢውም ክፍል ምን አስጨናቂና አስፈሪ ይሆናል የሚለውን ማወቅ መቻል አለብን፡ ፡ የመምህሩን ሚዛን ባይቀንስም በእኛው ተጨባጭ ሁኔታ ግን፣ ባዕዳንና መገናኛ ብዙሃናቸው ወያኔን እየደገፉ ባለበት በኢትዮጵያ የሚከሰተው እንኳን በዓለም አቀፍ ደረጃ በሀገራችንም የሚዳረስና የሚሰማ አይደለም። አንዳንድ ጥራዝ ነጠቆችም ሚሊዮኖች በቱኒዝያ የኮምፒዩተር ባለቤትና የኢንተርኔት ግልጋሎትም ተጠቃሚ በሆኑበት ይህ መሳሪያ በዚያ የተጫወተውን ሚና በኢትዮጵያ ለመድገም ብለው (!--ስንቱ ኮምፒዩተር አለው? ስንቱ ድረ ገፅና ራዲዮም ታፍኖ የለም?) በድረ ገፅ አማካይነት ያውም ቀነ ቀጠሮ ሰጥተው አመፅ ሲጠሩና መሳቂያ

ሲያደርጉን ቆይተዋል።

2/ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አመፅ ሊፈነዳ ተቃርቧል-- ግን ለኳሽን ይፈልጋል። ለዚህም ተቃዋ ሚ ነን የሚሉት ሀይሎች ወያኔን መለማመጥና የወያኔን ድንጋጌ ማክበር ትተው አለፍቃድ መሰለፍ፤ መስዋዕትንም በቀጣይነት እየከፈሉ መገኘት (የመንና ሶርያን ያጤኗል)፤ ድላቸውን ንም እንዳይቀሙ መዘጋጀት ይገባቸዋል። ወያኔ የሕዝብን ዕይታ ከአመፅ ወደ ሌላ ለማዛወር የሕዳሴ ግድብ የሚል ፊሊጥ ይዞ አባይን እንገድባለን ብለው የሚያቅራሩ አጫፋሪዎቹን አሰማርቷል። በቅርቡም ደግሞ በእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች የተወሰኑ የእገዳ ህጎችን አውጥቶ በዚሁ ውዝግብ ዙሪያ ሕዝብን ለመከፋፈል ተዘጋጅቷል። ሌሎች ደግሞ የአንድነት ወይም ኢትዮጵያዊ ሀይሎች የሕዝብን አመፅ በማቀነባበር ተግባተርና ተልዕኮ መሰመራተ ሲገባቸው ኢትዮጵያዊነታቸውን ደግመው ደጋግመው ከካዱ ተገንጣይ ሀይሎች ጋር ማበር አለብን የሚለል ጉንጭ አልፋና አደገኛ አቅዋም ይዘው በሀይሎች መሀል ንትርክና ክፍፍልን አስፍነዋል። ጋሬጣዎች ሁሉ መወገድ አለባቸው--ሀይሎችም ሕዝብም በወያኔ ላይ ሕዝባዊ አመፅን በማዘጋጀትና በመጀመር ላይ ማተኮር ይገባቸዋል ። የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ መዘናጋትን መደናገርን አይጠይቀንም--ሕዝባዊ አመፅን እንጂ! ፍርሀታችንን አሸንፈን፤ ክፍፍሉን አስወገድን በወያኔ ላይ ለአንዴም ለሁሌም እንነሳ እንጂ!